# የሰፊው ሕዝብ ድምፅ

ለሰፊው-ሕዝብ
(ወዛደሩ፣ ገበሬ፣ ነጋዴ፣ ወታደር፣ ምሁሩ፣)
መብትና ጥቅም
የሚታገል-ጋዜጣ


## የመላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ የተመሠረተበትን 11ኛ ዓመት ምክንያት በማድረግ ከመኢሶን ፖለቲካዊ ቢሮ የተሰጠ መግለጫ

ልዩ ዕትም

ነሐሴ 1971

ይህ የትግል ዘመን አልፍ መጥው ትውልድ መለስ ብሎ የዘመኑን ትግል ታሪክ በሚመረምርበት ጊዜ የኢትዮጵያ ተማሪዎች በመራራ ትግላቸው የፃፉት ገፅ በኢትዮጵያ ጭቁኖች የትግል ታሪክ ውስጥ አሸብርቀው ከሚታዩት ገፆች አንዱ እንደሚሆን አንጠራጠርም:: ባለፉት ዘመናት የኃይለ ሥላሴን አገዛዝ ከተለያዩ አቅጣጫዎች፣ በተለያዩ ቦታዎች በተበጣጠሩ ዓላማዎች እየተነሡ ያዋከቡትና ያዳከሙት ብዙ እንቅስቃሴዎችና ህዝባዊ ትግሎች ነበሩ:: ነገር ግን በተለይ ከሃያ ዓመታት ወዲህ በኢትዮጵያ የፖለቲካ መድረክ ላይ ብቅ ያለው አብዮታዊው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ ከነዚህ እንቅስቃሴዎች ሁሉ ዓይነተኛ የሚያደርጉት ጠባዮች ነበሩት:: በመጀመሪያ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ ከየአቅጣጫው፣ በየቦታውና በተበጣጠሩ ዓላማዎች ከተነሱት ተቃውሞዎች ዘለቅ እነዚህን ሁሉ በሚያስተባብሩ አጠቃላይ መፈክሮች ሥር የሚንቀሳቀስ አገር አቀፍ ንቅናቄ ነበር:: ሁለተኛ ደግሞ የኢት. ተማሪዎች ንቅናቄ ሃገራችን የደረሰችበትን የህብረተሰብ እድገት ደረጃ ጠንቅቆ ያወቀ፣ የፊውዳሊዝምንና የኢምፔርያሊዝምን ቀንደኛ ጠላትነት የተረዳ፣ እነዚህ ጥንድ ጠላቶች ከኢትዮጵያ ምድር ካልተደመሰሱ፣ ለሃገራችን ዕድገት ለኢትዮጵያ ጭቁኖች እርምጃና ነፃነት፣ እንደማይገኝ ጠንቅቆ የተገነዘበ አብዮታዊ ንቅናቄ ነበር:: እንደዚህም በመሆኑ በዚህች ምንም ዓይነት የተደራጀና አገር አቀፍ የሆነ የፖለቲካ ተቃውሞ ትግል በማታውቅ አገራችን የተማሪው ንቅናቄ አገር አቀፍነትና አብዮታዊነት፣ ሳለፈው የተማሪ ትውልድ ከሌሎች አገሮች የተማሪ ንቅናቄዎች የበለጠ ሃላፊነት ጥሎበት ቆይቷል:: ታጋይ ኢትዮጵያዊያን በኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ ዘላለማቸውን ሲኮሩ የሚኖሩት ይህ የተማሪ ትውልድ ይህንን ከፍተኛ ኃላፊነት በለጋ ትከሻው ላይ ተሸክሞ ታሪክ ለጣለበት አደራ ብቁ መሆኑን በማስመስከሩ ነው::

በነዚህ የትግልና የመስዋዕትነት ዓመታት ይህ የተማሪ ንቅናቄ የኃይለ ሥላሴ ፋሽስታዊ አገዛዝ ባሰለፈበት ፀረ ህዝብ ሀይል በምንም ሳይፈራ "መሬት ላራሹ" "ዲሞክራሲያዊ መብቶች" "የብሄረሰቦች እኩልነት"፣ "ብሄራዊ ነፃነት" እያለ ብዙ የከፈለበትን ትግል አካሄደ:: ነገር ግን ይህ ትግል ወደፊት እየገፋ ሲሄድና በአጠቃላይ

የሥርዓቱ እየበሰበሰ መሄዱ በያለበት የህዝቡን ትግል ሲያፋፍመው በተማሪው ንቅናቄ ውስጥ በግንባር ቀደምነት ለተሰለፈውና ማርክሲዝም ሌኒንዝምን እያዋሀደ የትግል መመሪያው ማድረግ ለጀመረው የመጀመሪያው የኢት. ማርክሲስት ሌኒንስት ትውልድ አንዳንዱ ነገሮች ግልፅ ሆነው መታየት ጀመሩ:: በመጀመሪያ እነዚህ ግንባር ቀደም ሀይሎች በመቀጠል ላይ ያለውን የኢትዮጵያ ጭቁኖች የነፃነት ተጋድሎ ከዳር እስከዳር አስተባብሮ ለመምራት ይችል ዘንድ ይህ ታጋይ ትውልድ ከተማሪው ንቅናቄ ባሻገር የመደራጀትን ጉዳይ ካሁኑ መያያዝ እንዳለበት ተገነዘበ:: ሁለተኛ ከላይ የተጠቀሱትን ዓላማዎች ከሥራ ላይ ለማዋል ለሚደራጁትና ለሚሰለፉት ሀይሎች ሁሉ የተጣራና አብዮታዊ አመራር ሊሰጥ የሚችለው ሃይል በማርክሲዝም ሌኒንዝም ርዕዮተ ዓለም የሚመራ ድርጅት መሆን እንዳለበት አመነበት::

ከዚህ እምነት በመነሳት በአገር ውስጥ፣ በአውሮፖ፣ በሰሜን አሜሪካና በቅርብ ምሥራቅ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ ውስጥ በግንባር ቀደምነት ከተሰለፉትና የድርጅትንም አስፈላጊነት ሆነ የማርክሲዝም ሌኒንዝምን መርህ ተቀብለው ትግሉን ከተማሪው ንቅናቄ ባሻገር ለመቀጠል በታሪክና በኢትዮጵያ ህዝብ ፊት ሃላፊነትን በተቀበሉ አብዮታውያን ኅትና በነሐሴ ወር 1960 ዓ.ም. በሃምቡርግ ከተማ በምዕራብ ጀርመን በተደረገው የመመስረቻ ጉባዔ ላይ የመላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ ተቋቋመ::

ይህ በስመ ጥሩው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ ውስጥ ተፀንሶ በጊዜው በሃገሪቱ የሚገኙትን ማርክሲስት ሌኒንስቶች አስተባብሮ የያዘው የመላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ ሲመሠረት ጀምሮ ዓላማዬ ብሎ የያዘው፣ ሰፊው የኢትዮጵያ ህዝብ በረዥም ጊዜ የትግል ታሪኩ ያገኘውን ቆራጥነትና ልበሙሉነት፣ ታታሪነቱንና በራስ የመተማመን ኩራቱን፣ ተመፀዋቾነቱንና በማንም ይሁን በማን ፊት የበታችነትን አሻፈረኝ ሲል የቆየ አመፀኛነቱን፣ በአጭሩ በዓለም ህዝቦች ሸንጎ የማይናቅ ማንነቱን በሚያድስበት የብሄራዊ ነፃነት ትግልና ይቺን አገር የሰላምና የእኩልነት የነፃነትና የብልፅግና ምድር በሚያደርጋት ህዝባዊ አብዮታዊ ትግል ውስጥ የግንባር ቀደም ድርሻውን ለማበርከት ነበር::

የመላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ ታጋዮች ገና በዚያ በሃይለ ሥላሴ ዘመን ይህንን ግልፅ ዓላማ ይዘው ሲነሱ ለዚህ ታላቅና ክቡር ግብ መጣጣኝ የሆነ መስዋዕትነትና ፈተና እንደሚጠብቃቸው ያውቁ ነበር:: ትግሉ መራራና ረዥም እንደሚሆን፣ ብዙ ውጣ ውረድ እንደሚያዘበት፣ መውደቅ መነሣት እንደሚፈራረቅበት ይገነዘቡ ነበር:: ስለሆነም አንዳንዴ እየበረደና ጠርቦ የተዳፈነ እየመሰለ፣ አንዳንዴ ደግሞ እየተፋፋፈ መንጊዜም መከሰምን ባያውቅ ለኢትዮጵያ ነፃነትና ክብር በሚደረገው በዚህ የማያቋርጥ ተጋድሎ ውስጥ አንዴ ይህንን የትግል ስልት፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ ያንኑን ታክቲክ እየተጠቀሙ ጊዜና ሁኔታን እያየ በሚለዋወጥ ስልት ምንም ጊዜና ምንም ሁኔታ ሊለውጠው በማይገባው ቆራጥነትና ታታሪነት መታገል አስፈላጊ መሆኑን አንድም ቀን ስተውት አያውቁም:: እንደዚህም በመሆኑ መሊሶን አብዮታዊ ጥራቱንና ወኔውን ምንጊዜም ከማይላሸቀው የታጋይ አባላቱ የሃገር ፍቅር ስሜት ጋር እያስተጋገዘ መዝኖና ፈቅዶ በጀመረው የትግልና የመስዋዕትነት ጉዳና ረዥም ጉዞውን ተያያዘው::

ነገር ግን ይህ የመጀመሪያ የኢትዮጵያ ማርክሲስት ትውልድ ለዚህ ዓላማ በዚህ ቆራጥነት ተደራጅቶ ትንሽ መራመድ እንደ ጀመረ መደቡቸውን ሙሉ በሙሉ ከድተው ከወዘአደሩና ከአርሶ አደሩ በተደባለቁትና የነፃነትን ትግል ረዥም ጉዞ ለመያዝ

በተነሳሱት አብዮታዊ ምሁራንና ከህዝቡና ከአብዮቱ ቀደመው በአቋራጭ ለሥልጣን በቋመጡ፣ የነፃነት ተጋድሎ የሰፊው ሕዝብ የረዥም ጊዜ ተጋድሎ ሳይሆን የጥቂት ግንባር ቀደም ነን ባዮች የአንድ ሰሞን ውርውር መስሏቸው በተቅበጠበጡ፣ ለዚህ ለመራራው ትግል መደባዊ ትዕግሥቱም ሆነ ወኔው፣ ኢትዮጵያዊ ሃገር ፍቅሩም ሆነ አብዮታዊ ጥራት ቱሉ ብሉ በከዳቸው "አጥር ዝላዮች" መካከል ከፍተኛ የመሥመር ትግል ተጀመረ:: በዚህ ትግል "የአጥር ዝላዮቹ" ክንፍ በመኢሶን ውስጥ ሥር መስደድ የጀመረውን ሃቀኛ መሥመር ማሸነፍ ስለ ተሳነው የዚህ የቀኝ ክንፍ ንዑስ ከበርቴ አዝማሚያ መሪዎች በነሐሴ ወር 1963 ዓ.ም. ከመኢሶን መገንጠላቸውን አስታወቁ:: ጥቂትም ቆይተው በሚያዝያ ወር 1964 ዓ.ም. በበርሊን ከተማ በኢትዮጵያ ጭቁኖች ትግል ውስጥ ታሪክ የማይረሳቸው ወንጀሎች ከፈፀሙ በኋላ እንደገለባ አሳት በገ ብሉ የጠፋውን "የኢትዮጵያ ህዝባዊ አብዮታዊ ፖርቲ" የተባለውን ስመ ጥሩ ድርጅት መሠረቱ::

በቀደመ አብዮት ኢትዮጵያ በተለይ በውጭ አገር ተማሪ መህበራት አማካኝነት ከየካቲት በኋላም በይፋ በመኢሶንና በኢህአፓ መካከል የተደረጉትን ትግሎች መላው የኢትዮጵያ ህዝብ ያውቃቸዋል:: በዚህ ትግል በመጀመሪያ ላይ ባላቸው "ዓይን ባቢ" መፈክሮችና በተሰበጣጠሩ ምክንያቶች ከተለያዩ የውጭ ሃይሎች በሚገርፍላቸው የማቴርያል ድጋፍ የተነሣ ኢህአፓ ገናና መስሎ ይታይ እንደነበር ማንም አይረሳውም:: ነገር ግን ይህ የአድሃሪያን ጊዜያዊ ማየል በሃቀኛ መሥመሩና በኢትዮጵያ ህዝቦች አያደር መንቃትና መደራጀት ተማምኖ ትግሉን ለቀጠለው መኢሶን አስደንጋጭ ነገር አልነበረም:: የኢትዮጵያ አብዮት ፍጥነት፣ የጭቁን ህዝቦቿ ከትግላቸው እየተማሩና እየነቁ መሄድ፣ ለመኢሶን የዚያኑ ያህል የዕድገትና የመለምለም ጉዳና ሲከፍትለት በዚያው ልክ ደግሞ በውጭ ሀይሎች የማቴሪያል ድጋፍ ከኢትዮጵያ ጭቁኖች የትግል ዕድገት ደረጃ ባልተጣጣመ ሁኔታ "አብጦ" የቆመው ኢህአፓ እየተዋረደና እየከሠረ ሄደ:: በአጭር ጊዜ ውስጥም ከለየላቸው ፀረ ሕዝቦች ጋር በመዳበል በአብዮቱ ላይ የኪሣራ ምልክቱ በሆነው ፀረ ህዝቡ አመፅ ተሰማርቶ የብዙ ሰማዕታት ደም የከፈልንበትን ግን ደግሞ ከአብዮታዊ አቋማችን አንዲት ስንዝር ፈቅ ያላደረገንን የሽብር ፈጠራ ዘመቻ ተያያዘው:: ይህ አኳሽ ምዕራፍ ግን የኢትዮጵያን አብዮት ወደፊት ከመራመድ፣ መኢሶንን ከመለምለም የኢህአፓንም ቅጥረኞች ወደ ታሪክ ትቢያ መጣያ እየተጓፉ ከመውረድ አላገዳቸውም::

በኢትዮጵያ አብዮት ሂደት ውስጥ ያለውንና በየጊዜው የሚቀያየረውን የሃይሎች አሰላለፍ እየመዘነ ታክቲኩን የሚቀይሰው መኢሶን በአንድ በተወሰነ የታሪክ ወቅት ንዑስ ከበርቴው ደርግ ያለውን የተወሰነ ተራማጅ ሚና በመገንዘብ በተለይ ከ1968 _ 1969 ከጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት ጋር ጊዜያዊ የትግል ህብረት በመፍጠር ሰፊው ህዝብ በንቃት በድርጅትና በትጥቅ ጉዳና ላይ እንዲገፋ ከፍተኛ ተጋድሎ አድርጓል:: ነገር ግን ይህ ንዑስ ከበርቴ ደርግ በኢትዮጵያ ጭቁኖች አብዮታዊ ትግል መገፋት ተደናግጦ የህዝቡን ሠፈር መከዳት ሲጀምርና ከርሱ በስተቀኝ ከነበሩ ሃይሎች ጋር ህብረት ፈጥሮ፣ የኢትዮጵያን ብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት እየከዳ፣ ብሄራዊ ነፃነታችንን ከከፍተኛ አደጋ ውስጥ እየከተተው ሲመጣ፣ መኢሶን ከጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት ጋር በቀለበሰ፣ በከህደትና በብሄራዊ ውርደት ጉዳና አልነጉደም:: በነሐሴ ወር 1969 ዓ.ም. የትግል ስልት ለውጥ በማድረግ ስፍር ቁጥር የሌላቸውን ሌሎች ጓዶችና ጓዲቶችን የሰዋበትን በኢትዮጵያ ጭቁኖችና በታሪክ ፊት ቃል የገባበትን ዓላማ አንግቦ የግንባር ቀደምነት ጉዞውን ቀጠለ::

በዚህ ወቅት ደግሞ የመኢሶንን ሀቀኛ አብዮታዊ መሥመር ለመዋጋት ሌሎች የታሪክ አተላዎች ተነሱ:: እየተጠናከረ በመጣው ፀረ አብዮት ፊት በመንበርከክ፣

አብዮትንና የእናት አገርን ክብር ለፍርፋሪ በመሸጥ በጠላት ፊት ካጎበደዱት የቀኝ አድርባይ ድርጅቶች ጋር ሌላ ዙር የመሥመር ትግል ተካሄደ:: ነገር ግን የሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ንቃት ከፍተኛ ደረጃ ላይ በሚገኝበት በዚህ ወቅት የቀኝ አድርባዮችን ጨርሶ ለማጋለጥ የጥቂት ወራት ትግል እንኳን አላፈጀም:: በዚህም ትግል የቀኝ አድርባዮች ልክ እንደ ኢህአፓ ሙሉ በሙሉ ርቃናቸውን ከቀሩ በኋላ ልክ እንደ ኢህአፓው "ዝመን" ደግሞ የኪሣራቸው ምልክትና የገብዐተ መሬታቸው ወግ በሆነው ፀረ ህዝብ አመፅ በአብዮቱ ሠፈር ላይ ተሠማሩ:: በመኢሶን አባላት ላይ ብቻ ሳይሆን በጠቀላላው በዲሞክራቶችና በአገር ወዳዶች ላይ ይህ ነው የማይባል ግፍና በደል ፈፀሙ:: ነገር ግን የመጀመሪያው ዙር ፀረ ህዝብ አመፅ መኢሶንን ከሃቀኛ መሥመሩ ፈቅ እንዳላደረገው ሁሉ ይኸኛውም በንዑስ ከበርቴው ደርግ፣ በአድሃሪው ቢሮክራሲና በቀኝ አድርባይ ድርጅቶች አማካኝነት በአብዮት ሠፈር ላይ የወረደው የእሥራት፣ የግርፋትና የርሸና ዘመቻ ለአብዮትና ለኢትዮጵያ ክብር ብሎ ከተያያዘው ትግል እንዲያፈገፍግ አላደረገውም:: ፀረ ህዝቦችንም ከኪሣራና ከታሪክ ትቢያነት እንዳላዳናቸውና እነርሱም ልክ እንደ ኢህአፓ በሰፊው ህዝብ ተተፍተውና የውርደት ማቅ ተከናንበው እንደከሰሙ በዚህ በያዝነው ዓመት የቀኝ አድርባይ ድርጅቶች ያጋጠማቸው ዕጣ አበጥሮ አሳይቶናል::

ዛሬ መኢሶን ሶስት ዓመት ሙሉ ከተለያዩ ፀረ ህዝብ ሃይሎች በተለያዩ ጊዜያት እየተፈራረቀ የወረደበትን አመፅ አልፎ፣ ድርጅታዊ ህልውናውን ሳያስደፍር በመዝለቁ ለኢትዮጵያ ክብርና ለአብዮታችን የቆሙ ሃቀኛ ኢትዮጵያውያን ሁሉ የሚኮሩበትና የሚመኩበት ድርጅት ነው:: ዛሬ ይህ ድርጅታችን እየወደቀና እየተነሣ ሳያቋርጥ ወደፊት የተራመደበትን የአሥራ አንድ ዓመት የትግል ጉዞ ዘወር ብሎ ሲቃኝ ብዙ የታሪክ ገፆች በታጋይ አባላቱ ደም የፃፈ መሆኑን እየተመለከተ በነዚህ ጓዶችና ጓዲቶች ፊት ተገቢ የሆነ ኩራት ይሰማዋል:: ዛሬም በብዙ ሺ የሚቆጠሩ የመኢሶን አባላት፣ ደጋፊዎችና ወገኖች ሁሉ በደርግ አሥር ቤት ቢማቀቁም፣ አያሌ የመኢሶን ግንባር ቀደም ታጋይ ጓዶችና ጓዲቶች ቢወድቁም፣ ደርግና ፀረ ህዝቦች ሲያልሙት ይኖራሉ እንጂ የነርሱ አርማ ከቶም አይወድቅም፤ አልወደቀምም:: በሚሊዮን የሚቆጠረው የኢት. ሰፊ ህዝብ ያነሳው አርማ ነውና:: በነዚህ ታጋይ አባላቱም ፊት ሆነ በጠቅላላው ለኢትዮጵያ ክብርና ነፃነት ሲከራከሩ በወደቁ ገበሬዎችና ወዛደሮች፣ መለዮ ለባሾችና ምሁራን፣ ወጣቶችና ሴቶች፣ ዲሞክራቶች አገር ወዳዶችና የጭቁን ብሄረሰቦች ታጋዮች ሁሉ ፊት "የነፃነት ትግል ይቀጥላል" እያለ መኢሶን የትግል ቃል ኪዳኑን ያድሳል:: ይህን ቃል ኪዳንበማክበር መኢሶን የወደፊት ትግሉን የሚቀይሰው ከዛሬይቱ ኢትዮጵያ ሁኔታ ከሚፈልቁ አንዳንድ መሠረታዊ ሃቆች ተነስቶ ነው:: እነርሱም የሚከተሉት ናቸው::

<u>አንደኛ፣</u> ዛሬ መኢሶንም ሆነ በጠቅላላው የኢትዮጵያ ህዝብ የቆሙላቸውና ያ ሁሉ ደም የተገበረላቸው የዲሞክራሲ፣ የእኩልነትና የብሄራዊ ነፃነት ዓላማዎች ገና ግባቸውን አልመቱም:: እርግጥ ከየካቲት 1966 ዓ.ም. ጀምሮ ተፋፍሞ በተካሄደው ትግል ብዙ ድሎች ተገኝተዋል:: ነገር ግን ከሁለት ዓመት ወዲህ በኢትዮጵያ ምድር የሚታየው ሃቅ በአብዮታችን መመሪያ የተዘረዘሩት ዓላማዎች አንቀፅ በአንቀፅ እየተሸሩ የኋሊት ጉዞ መጀመሩ ነው::በዚህ ሂደት ከተቀጠለ ዛሬ በተግባር የተሻረው የኢትዮጵያ ብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም በፀረ አብዮት ሃይሎች በይፋ እንደሚሻር መጠራጠር አይቻልም:: ስለሆነም ሰፊው የኢትዮጵያ ህዝብ፣ በከፍተኛ መስዋዕትነት ከተጎናፀፋቸው በኋላ የተነጠቁትን ድሎቹን መልሶ ለመጐናፀፍ እንደዚሁም

አዳዲስ ድሎችን ተጐናፅፋ ወደ ህዝባዊት ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ እንዲያመራ ትግሉን ማፋፋም አለበት:: በዚህ ትግል ውስጥ መኢሶን ገና በፕሮግራሙ ውስጥ "የኢትዮጵያ ጭቁኖች የሚያደርጉት የተበታተነ ትግል ከዳር እስከዳር አስተባብሮ የተጣራ አብዮታዊ አመራር ለመስጠት በታሪክ ፊት የተቀበለውን አደራ እስከ መጨረሻው ይጠብቃል" ባለው መሠረትና ከዚያም ወዲህ እየደጋገመ ባደሰው ቃል ኪዳኑ መሠረት በኢትዮጵያ ብሄራዊና ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ባንዲራ ሥር ትግሉን ይቀጥላል::

<u>ሁለተኛ፣</u> ምንም እንኳን ዛሬ በኢትዮጵያ ፀረ አብዮት አይሉ የብሄራዊ ክብራችን ፀር የሆኑ ሃይሎች በሃገራችን አንሠራፍተው፣ በሰፊው ህዝብና በወገኖቹ ላይ ከፍተኛ የሆነ ፀረ ህዝብ አመፅ ቢወርዱም መኢሶን፣ በአጠቃላይ ወቅቱ ለኢትዮጵያ ክብርና ነፃነት ለሚታገሉ ሃይሎች ያመች ነው ብሎ ያምናል:: ዛሬ የኢትዮጵያ ህዝብ እስኪያንገፈግፈው ድረስ ከመረረው ሥርዓት በትግሉ ተላቆ አዲሲቱን ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ መመልከት የጀመረበት ወቅት ነው:: መለኮን የቀየረ ሌላ ፀረ ህዝብ ፈላጭ ቆራጭነት፣ መለኮን የቀየረ ሌላ ብሄራዊ ውርደትና የአፍሪካ ሃፍረትነት በምንም ዓይነት አይሻም:: ከዚህ በተጨማሪ በመጀመሪያ ጊዜ በታሪኩ ከዳር እስከዳር የሚያውቀው፣ የተቀበለውና የተሰዋለት ሳይንሣዊ የሆነ መመሪያ አለው:: ስለሆነም በዚህ ላይ ነባዊ ፕሮግራሙ እየተመራ ለመጓዝ እስከፈለገ ድረስ በሱ የአብዮት ፍላጎት አንፃር የፀረ አብዮት ሃይሎች ማየል ዘላቂነት የለውም፣ በሱ የሃገር ፍቅር ስሜትና ወኔ አንፃር የጥቂት የታሪክ ጉድፎች ማየልም ዘላቂነት አይኖረውም:: ስለሆነም መኢሶን የኢትዮጵያ ማርክሲስት ሌኒንስቶች ዲሞክራቶችና አገር ወዳዶች ሁሉ ይህንን መሠረታዊ ሃቅ ተገንዝበው ተስፋ መቁረጥንና ውዥንብርን እየተዋጉ የነፃነቱን ትግል በአንድነት በግንባር ቀደምነት እንዲያፋፍሙ አብዮታዊና ብሄራዊ ጥሪ ያቀርብላቸዋል::

<u>ሶስተኛ፣</u> በዚህ የትግል ዘመን መጭው ጊዜ ለአብዮትና ለኢትዮጵያ ክብር ለሚታገሉ ማርክሲስቶች፣ ዲሞክራቶችና አገር ወዳዶች ሁሉ ይበልጥ አያመች እንደሚሄድም መኢሶን አይጠራጠርም:: ይህንን ሃቅ አለመቀበል የኢትዮጵያን አብዮት አንገብጋቢ ጥያቄዎች የህዝቡን የዲሞክራሲ መብቶች ጥያቄም ሆነ የብሄረሰቦችን የእኩልነት ጥያቄ፣ የብሄራዊ ነፃነታችንንም ሆነ ሌሎች የሰፊው ህዝብ ጥያቄዎች ታሪክ ያለፈው የቀኝ ሃይሎች ህብረት በሚገባ ይመልሳቸዋል እንደማለት ይቆጠራል:: ወይም ደግሞ የኢትዮጵያ ጭቁኖች ዲሞክራሲን ከቀመሱ በኋላ ወደ አዲስ ፀረ ህዝብ ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ፣ የአሜሪካን ኢምፔርያሊዝምን እያደከሙ ብሄራዊ ነፃነታቸውን መልሰው መጐናፀፍ ከጀመሩ በኋላ ወደ ሌላ አይነት ብሄራዊ ውርደት ሲነጉዱ አይናቸው እያየ ዝም ይላሉ እንደማለት ይቆጠራል:: ሁለቱም የአድሃሪያን የቀን ቅዠቶች ናቸው:: ከሃገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታም ከህዝቦቿም የሃገር ፍቅር ተጋድሎ ታሪክ ጋር የሚጣጣሙ አይደሉም:: እንደዚህም በመሆኑ የቀኝ ሃይሎች ህብረት ከዕለት ዕለት በክህደት ቁልቁለት እየተንቀለቀለ፣ ከዕለት ዕለት ይበልጡን ከሰፊው የኢትዮጵያ ህዝብ ህልምና ፍላጎት እየራቀ፣ በዚህም የተነሳ ከዕለት ዕለት በህዝቡ እየተተፋ ተቃውሞ እየናሰ ቀስ እንደሚሄድ ሳይታለም የተፈታ ጉዳይ ነው:: በዚህ ልክ ደግሞ ክህደትን አሻፈረኝ ብለው በሰፊው ህዝብ ወገን የፀኑ ማርክሲስት ሌኒንስቶች፣ ዲሞክራቶችና አገር ወዳዶች ሁሉ ምንም ያህል መስዋዕትነት ቢጠይቃቸውም መጭውን የመራራ ትግልና የመስዋዕትነት ብሎም የመጨረሻ ድል ዘመን የሚያያዙት በማይቀረው አሸናፊነታቸውና በዘላቂው ሃያልነታቸው ያላቸውን ፅኑ ዕምነት አድሰው ነው ማለት ነው::

....6

አራተኛ፣ ከነዚሀ ሃቆች በመነሣት ዛሬ የተመሠረተበትን 11ኛ ዓመት በሚያከብርበት ወቅት መኢሶን ለኢትዮጵያ ማርክሲስቶች፣ ዲሞክራቶችና አገር ወዳዶች፣ ያ ሁሉ ደም የተለገሠለት አብዮታችን መቀልበስ፣ የተደነቀው የብሄራዊ ነፃነታችን ታሪክ መጉደፍ ሳንገበገባቸው ኢትዮጵያውያን/ት/ ሁሉ በሰፊው ህዝብ ድምፅ ቁ. 69 ያቀረበውን ጥሪ ያድስላቸዋል፡፡ የኢትዮጵያ አብዮት ከግቡ መድረስም ሆነ የብሄራዊ ነፃነቷን መከበር የመሰለ ቁም ነገር የኔ ብቻ ታሪካዊ አደራ ነው ብሎ የተመፃደቀበት ወቅት በመኢሶን የትግል ታሪክ ውስጥ አይገኝም፡፡ የመኢሶን አላማ እርሱ ለቆመለት የአብዮትና የብሄራዊ ነፃነት ዓላማ የቆሙ ሁሉ ተባብረው በሁላችንም ትግል የሁላችንም የሆነች ህዝባዊት ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ ለመመሥረት በሚደረገው ትግል የበኩሉን አስተዋጽኦ ለማድረግ ነው፡፡ ስለሆነም ይህ የጋዜ አንድነት ካምናው ይልቅ ዘንድሮ በይበልጥ በሥራ እንዲተረጎም፣ የኢትዮጵያ ገበሬዎችና ወዝአደሮች፣ መለዮ ለባሾችና ምሁራን፣ ወጣቶችና ሴቶች፣ አገር ወዳድ የጦርና የፖሊስ መኮንኖች /በደርጉ ውስጥ የቀሩት ጭምር/ ዲሞክራቶችና የጭቁን ብሄረሰብ ታጋዮች ሁሉ ጥቃቅን ልዩነታቸውን አቻችለው በዋናው ቁም ነገር ማለትም በኢትዮጵያ አብዮትና ብሄራዊ ነፃነት ጉዳይ ላይ እንዲሰበሰቡ፣ ሌሎች ታጋዮች ቀደም ሲል የወደቁለትን የኢትዮጵያ ብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም አርማ ይዘው በሕብረት ወደፊት እንዲጓዙ አብዮታዊና ብሄራዊ ጥሪውን ያስተላልፍላቸዋል፡፡

የመኢሶን ሰማዕታት አርማ አልወደቀም!

ከፕሮግራማችን ጋር ወደፊት!

አብዮታዊት እናት አገር ወይም ሞት!

የነቃ የተደራጀ የታጠቀ ህዝብ ትግል ያሸንፋል!

— የመላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ —
ማዕከላዊ ኮሚቴ

## "መስከረም 2" አምስተኛው አመት

የኢትዮጵያ ተማሪዎችና ምሁራን አብዮታዊ ንቅናቄ፣ የኢትዮጵያ ጭቁን ብሄረሰቦች ለእኩልነትና ለመብታቸው ያካሄዱት ትግል፣ የኢትዮጵያ አርሶ አደሮች ለመሬትና ለነፃነት በየቦታው ያደረጉት ገብታዊ ትግል፣ የኢትዮጵያ ወዛደር መደብ በየጊዜው ያደረገው ተጋድሎ፣ ዲሞክራትና ሃገር ወዳድ መለዮ ለባሾች ያደረጉት አብዮታዊ የትግል ክንተፍ፣ በጠቅላላው የኢትዮጵያ ሰፊ ህዝብ ፊውዳሊዝምንና ኢምፔርያሊዝምን ለመደምሰስ ያደረገው አብዮታዊ ትንንቅ፣ በየካቲት 1966 ከአጽናፍ እስከ አጽናፍ ምድሪቷን ያንቀጠቀጠ አብዮታዊና ህዝባዊ እንቅስቃሴን አስነስቶ ነበር:: ይህ ህዝባዊ ዲሞክራሲያዊ እንቅስቃሴ፣ ለዘመናት የኢትዮጵያ ሰፊ ህዝብን በፋሽስታዊ አመፅ ረግጦ የገዛውን፣ የበሰበሰው የፊውደ ፋሺስቶ የሃይለ ሥላሴ መንግሥትን ከውድቀት አፋፍ ላይ ጥሎት ነበር::

በነፁህ የሃገር ወዳድነት ስሜት ከኢትዮጵያ ሰፊ ህዝብ ጋር በወቅቱ አብሮ "መሬት ላራሹ"፣ "ዲሞክራሲያዊ መብቶች"፣ "የብሄረሰቦች እኩልነት"፣ "እውነተኛ ብሄራዊ ነፃነት" በማለት አብዮታዊ ትግል ያደርግ የነበረው የኢትዮጵያ የምድር ጦር የአየር ሃይልና የፖሊስ ሠራዊት አስተባባሪ ደርግ፣ በመስከረም 2 1967፣ የጭቆናና የምዝበራ፣ የብሄራዊ ውርደትና ቅሌት ምልክት የነበረውን የፊውደ- ፋሽስት መንግሥትን ቀንጮ፣ ሃይለ ሥላሴን ከዙፋኑ አወረደ:: ይህ በየካቲት 1966 የተቀጣጠለው ህዝባዊ አብዮታዊ እንቅስቃሴ፣ አንድ ከፍተኛና የመጀመሪያው ድል ነበር:: የኢትዮጵያ ጭቁኖች በሙሉ ይህን ቀን በትግል ታሪካቸው ውስጥ፣ የወደፊት የዲሞክራሲ፣ የፍትህና የእውነተኛ ብሄራዊ ነፃነት ጮራ ጭላንጭል የተመለከቱበት በመሆኑ፣ እንደአንድ የትግል ምዕራፍ መከፈቻ የመለከቱታል::

በመስከረም 2 1967 ፋሽስቱ ሃይለ ሥላሴ ሲወድቅ፣ የኢትዮጵያ ሰፊ ህዝብ በየካቲት ወር የዲሞክራሲና የፍትህ፣ የብሄረሰብ እኩልነት፣ የመሬትና የነፃነት፣ የብሄራዊ ክብርና ነፃነት መፈክሮችን አንግቦ ለተነሣበት ትግል አዲስ ምዕራፍ መክፈቻ እንጂ ማብቂያ አድርጉ እንዳልተመለከተው ግልፅ ነው:: ስለሆነም ከዚህ ቀን አንስቶ ያለፉት አምስት አመታት ብዙ መስዋዕትነት የተከፈለበት፣ ብዙ ውጣ ውረድ የበዛበትና ከፍተኛ ድሎች የተቀዳጀባቸው፣ በሎም አብዮታዊው ትግሉ እየገፋ ሲሄድ ቋሚ ወዳጅንና ጠላትን ሰፊው ህዝብ ለመለየት የቻለበት ከፍተኛ የመደብ ፍልሚያ የነበረበት ዓመታት ናቸው::

ባለፉት አምስት አመታት የተገኘ አንድ ትልቅ ትምህርት ሰፊው ህዝብ በአደረጋቸው ትግሎች የተቀዳጃቸውን ድሎች ሳለማስነጠቅ ዋናው አስተማማኝ ሃይል በእርሱ ስም የሚመፃደቅ ማንም ሌላ ሃይል ሳይሆን፣ እራሱ ሰፊው ህዝብ የፖለቲካ ሥልጣን ባለቤት ሲሆን ብቻ መሆኑን ነው:: ሰፊው ህዝብ የፖለቲካ ሥልጣን ባለቤት የሚሆነውም በሰላምና በስምምነት ወይንም በአንዳች ሌላ ዘዴ ሳይሆን፣ በረዥሙና መራራ ትግል ብዙ መስዋዕትነት ሊከፈልበት በሚችል ከፍተኛ ተጋድሎ፣ በመደብ ፍልሚያው ውስጥ፣ በህዝባዊ አመፅ አማካይነት የፖለቲካ ሥልጣን ሲነጥቅ ብቻ ነው::ይህን ያለፈው አጭሩ የአምስት አመት የኢትዮጵያ ሰፊ ህዝብ የትግል ልምድ ያሳየው ሃቅ ነው::

ሃይለ ሥላሴ ከዙፋኑ ከወደቁበት ጊዜ አንስቶ ያለፈውን የትግልና የመስዋዕትነት ጊዜ ዞር ብለን ብንመለከት፣ በአንድ ፊት አያሌ ድሎች የተጎናፀፍንባቸው፣ የዲሞክራሲና የእውነተኛ ብሄራዊ ነፃነት ጭላንጭል ማየት የጀመርንበት ሁኔታን እናስታውሳለን፣ በሌላ በኩል ደግሞ ዛሬ የደረስንበት፣ ዲሞክራሲ የታፈነበት፣ ፍትህ የተረገጠበት፣ ኢትዮጵያ ወደ ብሄራዊ ውርደትና አዘቅት የተሸቆለቆለችበት፣ በአጠቃላይ የተገኙት ድሎች እየተቀለበሱ የወታደራዊ መንግሥት ፈላጭ ቆራጭነት የተንሠራፋበት ሁኔታ ውስጥ መገኘታችን እንረዳለን::

የ1967 ዓመት በሃገር ወዳድነት ስሜት በመገፋት ብቻ ሃይለ ሥላሴን ከሥልጣን ያወረደው ንዑስ ከበርቴው ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ በአብዮትና በፀረ አብዮት መካከል የሚዋልልበት፣ ይሁንና በውስጡ የነበሩ የወቅቱ ተራማጅ ሃይሎች የሰፊውን ህዝብ ወገን መርጠው አብዮታዊ ትግል ያካሄዱበት ወቅት ነበር::

1968 በደርጉ ውስጥ የነበሩት የወቅቱ ተራማጅ ሃይሎች የበላይነት የነበራቸው ወቅት፣ በመሆኑም በመኢሶን ግንባር ቀደም ትግልና በሰፊው ህዝብ አብዮታዊ እንቅስቃሴ መገፋት ከፍተኛ ህዝባዊ ድሎች የተገኙበት ዓመት ነበር:: የኢትዮጵያ የፊውዳል ሥርዓት ማህበር ከሥር መሠረቱ ያናጋው ከመሬት ላራሹ አዋጅ አንስቶ፣ እስከ ሳይንሳዊው የአብዮታችን መመሪያ፣ የብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ድረስ የታወጀበት አመት ነበር::

1969 መኢሶን፣ ሌሎች ማሌና ተራማጅ፣ ዲሞክራሲያዊና አብዮታዊ ሃይሎች አብዮታችን ከሚፈታተኑት፣ ደርግ ውስጥ ከነበሩት ፀረ ህዝቦች ጭምር ከኢህአፓ ከኢዲዩና ከሌሎች ፀረ አብዮተኞች ጋር በተለይ በትግሉ ውስጥ በግንባር ቀደምነት የተሳተፈው መኢሶን ብዙ መስዋዕትነት የከፈለበት የአብዮትና የፀረ አብዮት ትንንቅ የተካሄደበት ወቅት ነበር:: ሰፊው ህዝብ በድል አድራጊነት በመውጣት የመኢሶንን የነቃ የተደራጀና የታጠቀ ህዝብ ትግል የፖለቲካ መሥመር አንግቦ የተጋደለበት ከፍተኛ የመደብ ፍልሚያ ወቅት ነበር::

በሌሎች አብዮቶችም እንደታየው፣ የሰፊው ህዝብ አብዮታዊ እንቅስቃሴ ሲገፋ ከርሱ በስተኋላ መዳከርና ከቀኝ ሃይሎች ጋር ማበር ጠባዩ የሆነው የፖለቲካ ሥልጣን የጨበጠ የንዑስ ከበርቴው መደብ በኢትዮጵያም ከ1969 ዓ.ም. አጋማሽ አንስቶ ይህ በሽታ ተፀናውቶት ነበር:: ስለሆነም መኢሶን በ1968 የሰፊው ህዝብ ዋና ጠላት የሆኑትን ፊውዳሊዝምንና ኢምፔሪያሊዝምን ለመዋጋት ከ.ወ.አ. ደርግ ጋር የመሠረተውን ጊዜያዊ የትግል ህብረት በ1969 መጨረሻ ላይ ሠርዞ የትግል ስልት ለውጥ አደረገ::

መኢሶን ወገናዊነቱና አንድነቱ ምንጊዜም ከሰፊው ህዝብ ጋር በመሆኑ፣ የዲሞክራሲ፣ የብሄራዊ ነፃነትና የአብዮታዊ አመራር መፈክሩን አንግቦ ነፃ ህዝባዊና አብዮታዊ እንቅስቃሴን ማካሄድ ቀጠለ:: 1970ን በአብዮታችን ውስጥ አይነተኛ የሚያደርገው በአንድ በኩል የታሪክ አተላ የሆኑ ቀኝ አድርባዮች፣ የፖለቲካ ሥልጣኑን ለማደላደል የመረጠው ጊ.ወ. መንግሥትና ፀረ አብዮት ሃይሎች በአዲሱ ህብረታቸው አማካይነት በኢትዮጵያ አብዮትና ሰፊ ህዝብ ላይ መነሣታቸው ነው:: በሌላ በኩል ደግሞ መኢሶን፣ ሌሎች አብዮታውያን፣ ዲሞክራቶችና አገርወዳዶች ከለየላቸው ፀረ ህዝብና ፀረ አብዮት ሃይሎች ጋር በዲሞክራሲ፣ በብሄራዊ ነፃነትና በአብዮታዊ አመራር

አርማ ሥር ያደረጉት ትግል፣ ጊ.ወ. መንግሥት የተያያዘውን የክህደት ጎዳና ለመቋቋም ያካሄዱት አብዮታዊ እንቅስቃሴ ነው:: በአጭሩ 1970 አዲሱ የቀኝ ሃይሎች ህብረት የተቋቋመበት በመሆኑ፣ የዛሬውን ፀረ ዲሞክራሲያዊ አገዛዝ፣ የዛሬውን የኢት. ብሄራዊ ነፃነት መደፈር፣ የዛሬውን ብሄራዊ ውርደትና ቅሌት፣ የዛሬውን ቢሮክራሲያዊ የወታደራዊ መንግሥት ፈላጭ ቆራጭነት እንዳያስከትል፣ በአጠቃላይ የብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራማችን እንዳይቀለበስ በመኢሶን ግንባር ቀደምነት መስዋዕትነት የተሞላበት ህዝባዊ አብዮታዊ ትግል የተካሄደበት አመት ነበር:: ይሁንና የሰፊው ህዝብ ወገን ከማጥቃት ወደ አቻነት፣ ከአቻነት ወደ መጠቃት ተሸጋገር፣ በተለይም የአዲሱ የቀኝ ሃይሎች ህብረት ፊታውራሪ በነበሩት፤ ዛሬ የታሪክ ቆሻሻ መጣያ ውስጥ በወደቁ የቀኝ አድርባይ ድርጅቶች የክህደት ምርጫ የተነሣ፣ ብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራማችንን ከመቀልበስ ለማዳን፤ ጊ.ወ. መንግሥት የተያያዘውን የፀረ ዲሞክራሲና የብሄራዊ ውርደት ሂደት ለመግታት አልተቻለም:: የ1970 አብዮታዊ ትንንቅ ከመኢሶን ብዙ መስዋዕትነት የጠየቀ ተጋድሎ ነበር:: ትግሉ ግን ይበልጥ መራራና ረዥም ሆነ እንጂ አልቆመም አይቆምም::

1971 አዲሱ የቀኝ ሃይሎች ህብረት የተደላደለ የመሠለበት፣ ቢሮክራሲያዊው ወታደራዊ መንግሥት ፀረ ዲሞክራሲን ያነገሠበት፣ ኢትዮጵያን ጠቅላሉ በብሄራዊ ውርደት ጎዳና ይዞ የነጎደበት፣ የኢትዮጵያ ሰፊ ህዝብ ብዙ መስዋዕትነት ከፍሎ ባስወጣው የአሜሪካን ኢምፔርያሊዝም እግር ሌላ ሀያል መንግሥት ኢትዮጵያን ተቀጥያ ያደረገበት፣ የራስ በራስ መተማመን መርሆች በጣም የተረገጡበት፣ በአጠቃላይ ደግሞ ወታደራዊ ፈላጭ ቆራጭነት የነገሠበት ዓመት መሆኑ፣ እንኳን መኢሶን፣ እንኳን ዲሞክራቶችና ሃገር ወዳዶች ቀርቶ በቆሰበሰበው ላይ የመፈከር አውራጅ የሆነ ቢሮክራት ሁሉ የማይክደው ሃቅ ነው:: ከዚህ ጋር ተያይዞ ግን 1971 ያሳየን ኮመዲ ቢኖር 1970 የቀኝ ሃይሎች ህብረት ፊታውራሪ የነበሩት ምስኪን የቀኝ አድርባይ ድርጅቶች ከነ "ኢማሌድሃቸው" የታሪክ ትቢያ ሆነው እንደተመጠጠ ሎሚ መወርወራቸው ነው:: ይህ ሁሉ ሲሆን መኢሶንና ሰፊው ህዝብ ከአለፈው ትግላቸው ብዙ እንደውሃ የጠራ ልምድና ትምህርት ቀስመው አልፈዋል::

ዛሬ ሃይለ ሥላሴ የወደቁበትን አምስተኛ አመት እንደ እንቱ የየካቲት አብዮታዊ እንቅስቃሴ ዱል ሰናስበው፣ ያለፉት አመታት ብዙ የአብዮትና የፀረ አብዮት ድርጊቶች የተከናወኑበት መሆኑን እንረዳለን:: ባለፉት አምስት አመታት መኢሶን ጊዜውና ሁኔታው በሚጠይቀው ልዩ ልዩ አብዮታዊ የትግል ዘዴ በመጠቀም ከሰፊው ህዝብ ጎን ሆኖ በቆራጥነት መታገሉን አሳይቷል:: ሆኖም ሰፊው ህዝብ ገና በድል አድራጊነት አልወጣም:: በድል አድራጊነት የሚወጣውም ገና መራራና ረዥም አብዮታዊ ትግል ከአካሄደ በኋላ ብቻ መሆኑን እንረዳለን:: ለዚህ ትግልም መጭው ጊዜ ብሩህና ለትግል ቆርጦ ለተነሣ አብዮታዊ ሃይል ሁሉ ያመቺ መሆኑን እንጠራጠርም::

......10

በየካቲት የተነሣሣበት የዲሞክራሲ ጥያቄ ቀርቶ፣ የብሄረሰብ እኩልነት መብት ጥያቄ በትምክህተኝነት ተተክቶ፣ የሃገር ፍቅርና የሃገር ወዳጅነት ስሜት በብሄራዊ ውርደትና አጎብዳጅነት ተሸሮ፣ በ1967 ሃይለ ሥላሴን ከዙፋኑ ያወረደው የያኔው ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ በኢትዮጵያ ቢሮክራሲያዊ ፈላጭ ቆራጭ ወታደራዊ አገዛዝን አንሰራፍቶአል። ሃገሪቱን የተራማጆች የዲሞክራቶችና ሃገር ወዳዶች እሥር ቤት አድርጓታል፡፡ የአብዮታዊ ምሁራን፣ የማሌያችና የተራማጆች መረሸኚያ መድረክ አድርጓታል፡፡ ሰፊው ህዝብ ተቀዳጅቶ የነበራቸው ህዝባዊ ድሎች እየተነጠቁ ናቸው፡፡ በአጠቃላይ የብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራሞችን በተግባር ተቀለብሷል፡፡

ስለሆነም የወደፊት ትግላችን በአጠቃላይ የተነጠቁት አብዮታዊ ድሎችን የፈለገውን መስዋዕትነት ቢጠይቅም ለማስመለስና ለከፍተኛ ድሎችም ረዥሙንና መራራውን ተጋድሎ መያያዝ ነው፡፡ ብሎም የኋላ ኋላ ህዝባዊትና ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን መመሥረት ነው፡፡ ለዚህ የረዥም ጊዜ ዓላማችን የወቅቱ ዋናው የመኢሶን ጥሪ ለዲሞክራሲ ለእውነተኛ ብሄራዊ ነፃነትና ክብር የቆሙ አብዮታዊ ሃይሎች በሙሉ የትግል አንድነት እንዲመሠርቱ ነው፡፡ የመኢሶን ጥሪ አሁንም በቅጥር 69 ያስተላለፈውን የትግል አንድነት ጥሪ እንደገና ደጋግሞ ማደስ ነው፡፡

— የሃቀኛ ተራማጆች፣ የዲሞክራቶችና የሃገር ወዳዶች የትግል አንድነት ይኑር!

— ከብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ጋር ወደፊት!

— የመኢሶን ሰማዕታት አርማ አይወድቅም!

— የነቃ የተደራጀ የታጠቀ የህዝብ ትግል ያሸንፋል!